# ምፅዐት ለምኑ

ከአብርሃም በየነ

ታሪኩን ባህሉን
ጠብቆ ለመኖር
በራስ መተማመን
በችሎታ መፍጠር፣
አድጎና በልፅጎ
በገበያ ውድድር፣
በእኩልነት ሚዛን
እንደ ህዝብ እንዳገር፣
ሰንደቅ አውለብልቦ
ተላብሶ ነፃነት፣
መኖር ካልተቻለ
በልዕዋላዊነት፣
የናሙና ስዕል
ቀልሞ በካርታ፣
በሃያላን ትዕዛዝ
ፈቃድ ወይ ችሮታ፣
ለሚገፋው ህይዎት
ዓለም መጨነቁ፣
ምን ቢሆን ነው
ተስፋው
የቅርቡ የሩቁ?
እንደ እናት
ኢትዮጵያ፣
እንደ የጎዝላቪያ፣
እንደ ገሬናዳ
ወይ እንደ ፓናማ፣
እድሉ ሲወሰን
በያንኪ ፓርላማ፣
ድህነቱን በልቶ

ባርነቱን ለብሶ፣
ደካማ የት ሊደርስ
ቢራመድ ገስግሶ?
ዕድገቱ ልማቱ
ሰላም የማስፈኑ፣
ፈቃድ ካልተቸረው
ካንግሎ ሳክሰኑ፣
ጠግቦ ለማያድረው
ለማይቀናው ጎኑ፣
በሶስተኛው ዓለም
ለሚጥመነመኑ፣
የኖህ ዘመን ይውረድ
መፅዐት ለምኑ።
ፅዋችን እንዲሆን
የጋራ ዕጣ ፈንታ፣
ዓለም ቁና ትሁን
ላሽከርም ለጌታ፡፡
ገዳዮችም ጭምር
መሞትን እንዲያውቁ
ምድርና ሰማይ ይደበላለቁ።
ምድር ህጉን ሽሯል
የላዩ ይጠራ፣
ይበጠር ይንጠርጠር
ሰዶም ከገሞራ፣
ይግባ በሞት ሰፌድ
ሃጣኑ ፃድቃኑ፣
ዓለም ትደባለቅ
ምፅዐት ለምኑ።